በተጠየቀውም ገንዘብ ላይ ተጠሪ ክርክር ስለሌው ይህንኑ በክስ የተጠየቀውን ብር 55,068.56 /አምሳ አምስት ሺህ ስልሳ ስምንት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 24704

ኀዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ሐጎስ ወልዱ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ
አቶ ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት-ጠበቃ አቶ ኃይሉ ተሰማ-ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ ጤና ቢሮ ዐ/ሕግ አቶ ተመስገን መንግሥቴ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የመድን ዋስትና ውል ስለመኖር የሚመለከት ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ክስ በአሰላ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሠረተው የአሁኑ አመልካች ሲሆን የክሱ ይዘትም ባጭሩ የተጠሪ ንብረት የሆኑ ሁለት ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ጥር 2 ቀን 1995 በደብዳቤ ቁጥር 2915/73/9 በጠየቀው መሠረት አመልካች ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የሰሌዳ ቁ. 4-28437 ቶዮታ ኮብራ የሆነው የተጠሪ መኪና እ.ኤ.አ. ከ13/3/93 ጀምሮ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን ውል በፖሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/0727/03 ተሰጥቶት፣ ለዚህም አገልግሎት አረቦን ብር 11,510.00 /አሥራ አንድ ሺህ አምስት መቶ አሥር ብር/ ተጠሪ ባለመክፈሉ በፍርድ እንዲወሰንበት ሲል ክስ ያቀረበ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም የተጠሪን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር ካዳመጠ በኋላ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበውን የመድን ዋስትና ውል

አለመኖር የተመለከተ ክርክር ከቀረበው የግራ ቀኝ ማስረጃ አንፃር ከመረመረ በኋላ የመድን ዋስትና ውሉ ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1727/1/ የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ መኖር እንዳለበት እና ይህም በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት መሆኑን ሕጉ የሚያስገድድ ሆኖ እያለ በአመልካች በኩል የቀረበው ማስረጃ ይህንን እና ሌሎች የሕጉን ድንጋጌዎች ስለማያሟላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውል ተቋቁሟል ለማለት እጅግ አዳጋች ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህንን ውሣኔ መቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍረድ ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ለሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ይህንን ውሣኔ የሚቃወም ሲሆን አመልካች ያቀረባቸው የአቤቱታ ነጥቦች፣ የመድን ውል አመሠራረት የሚረጋገጠው በንግድ ሕጉ በተደነገገው እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ አይደለም፣ ይህም ሲባል በጉዳዩ ላይ ልዩ ሕግ እያለ የጠቅላላ ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት አድርጎ የመድን ውል የለም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ እንዲሁም የምስክሮች ፊርማ መኖር ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑን የንግድ ሕጉ አያመለክትም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የመድን ውል አመሠራረትን በተመለከተ የወሰዱት አቋም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም ሲል ጠይቋል፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ በሕግ የተደነገገውን የመድን ውል ፎርም አያሟላም በሚል አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቦ አከራክሯል፡፡

የተጠሪ መ/ቤት ተወካይ የክልሉ ፍ/ቢሮ በአቤቱታው ላይ ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ የመድን ውል በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ካልተፈረመና በምስክሮች ካልተረጋገጠ ሕጋዊ ውጤት እንደሌለው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1675 እና የንግድ ሕግ አንቀጽ 659/1/ ያስገነዝባል፡፡



አመልካች የመድን ውል አለ በማለት ያቀረበው ማስረጃ የተጠሪ መ/ቤት ማኅተምና ፊርማ የሌለው በመሆኑ አመልካች ብቻውን ያዘጋጀው ውል ተጠሪን ስለማያስገድድ የመድን ውል ሳይኖር የመድን ውል ግዴታ የለም በማለት በሥር ፍ/ቤት ያቀረበውን ክርክር አጠናክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡

አመልካች ግንቦት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ባቀረበው የመልስ መልስ በተጠሪ የቀረበው የመድን ዋስትና ሽፋን ጥያቄ እና በአመልካች የተሰጠው የመድን ውል ፖሊሲ በጋራ ሊታዩ ይገባል በማለት አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚያሻው የሕግ ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሠነድ ልውውጥ ስለ ኢንሹራንስ ውል አፃፃፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ አሟልቷልን? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የሕጉን ይዘት ከመመርመራችን በፊት በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ንብረትነታቸው የተጠሪ ለሆኑት ሁለት መኪኖች የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በተጠሪ መ/ቤት ማኅተም እና በሚመለከተው ሁለት ፊርማ መጠየቁ አመልካች ለአንደኛው መኪና የመድን ሽፋን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ የመድን ውል ፖሊሲ ለተጠሪ መስጠቱ ነው፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የእነዚህ ሁኔታዎች መኖር በራሱ የኢንሹራንስ ውል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል መመሥረቱን ያረጋግጣልን? የሚለው ነው፡፡

የመድን ውል ስለመኖሩ ለማስረዳት አመልካች ያቀረበውን ማስረጃ ከፍተኛው ፍ/ቤት ሲመረምር መሠረት ያደረገው በፍ/ብ/ሕግ ስለውሎች አጻጻፍ ፎርም የተመለከተውን ድንጋጌ ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አጥብቆ የተከራከረው የውሎችን አመሠራረት የሚመለከቱ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌዎች ከመሆኑ የተነሣ ይመስላል ከፍተኛው ፍ/ቤት ትኩረት የሰጠውና ለውሣኔው መሠረት ያደረገው የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1719 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች

ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በጥቅሉ መሠረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1725/ለ/ እና 1727/2/ መሠረት የኢንሹራንስ ውሎች በጽሁፍ መደረግ እንዳለባቸው በጽሁፍ የሚደረጉትም በምስክሮች ፊት መሆን እንዳለበት ይህ ካልተፈፀመ ውሉ እንደማይፀና የሚያስገነዝቡ ናቸው የሚለውን የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የኢንሹራንስ ውል አመሠራረት እና የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 1725 እና 1727 ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወሰን እንዲሁም የንግድ ሕግ ስለ ኢንሹራንስ ውሎች የተመለከተውን ድንጋጌ ቁጥር 657 እና ተከታዮቹ በተመለከተ የሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 23003 ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ አሁን ከተያዘው ጉዳይ እና ጭብጥ ጋር ተመሣሣይ ሆኖ ስላገኘነው ከዛው ውሣኔ አንፃር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የመድን ሽፋን ለአንድ ዓመት በመሆኑ የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23003 በወሰደው አቋም መሠረት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡ /የሰበር መ/ቁ. 23003 ይመለከቷል/

ስለዚህ ተጠሪ የመድን ሽፋን እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት አመልካች ለአንድ ዓመት የሚቆይ የመድን ሽፋን በፖሊሲው ፎርሞ የሰጠው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እና የፖሊሲው ይዘት በንግድ ሕግ ቁጥር 654, 657 እና 658 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘት ያሟላ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት ያልተካደ በመሆኑና እነዚህ አንቀጾች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ሽፋን መኖሩን ለማረጋገጥ በቂ ሆነው ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1725 እና 1727ን መሠረት በማድረግ በሁለቱ መካከል የመድን ውል አልተመሰረተም በማለት ተጠሪ የጠየቀውን አረቦን እንዳይከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



## ው ሣ ኔ

1. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በፓሊሲ ቁጥር NK/1/MTPV/07 27/03 በተሰጠው የመድን ፖሊሲ ውል መሠረት ለአንድ ዓመት የቆየ የመድን ውል ተመስርቷል ብለናል፡፡
2. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 816 መጋቢት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39792 የካቲት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመድን ውል መኖር ስለተወሰነ በአረቦን አከፋፈል ላይ ፍ/ቤቱ የመሠለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ